# በሕዝብ ትግል መቀለድ ያብቃ! ትግላችን ኮምፓሱ የጠፋበት መርከብ እንዳይሆን

ተካልኝ አባለ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አዲስ ምዕራፍ ይዞ ድሉን ሊያበስር ሲነሳ በአላዋቂ ሳሚነትና በወያኔ ቅጥረኛነት ይህን ትግል ሊያደናቅፉ የተነሱ በዝተዋል። የሚያሳዝነው ወይም የሚያደናግረው እነዚህ ክፍሎች የሕዝብ ወገን መስለው ሊቀርቡ መነሳታቸው ነው።

ጉዳዩ ባለፈው ሰሞን ብዙ ሕዝብ በተካፈለበት ፓል ቶክ ውይይት ተነስቶ ነበር። የሚሰማ ካለ እንግዳው የሰጡት "የትግላችን ምሥጢር የባቂላ ወፍጮ አይሁን" ምክራቸው ወቅታዊ ነው። የሕዝብ ትግል መቀለጃ ወይም የትግል ትርጉም ባልገባቸው ሰዎች በዘፈቀደ መጨፈሪያ ሊሆን አይገባውም። ትግል አሰናካይ ድርጊቶችንም የሚፈጽሙ ሰዎች ተው እንጂ መባል አለባቸው። ከወያኔ ጋር የሚደረገው ትግል የሚያስከፍለው ዋጋ ቀላል አይደለም እና። ቢያንስ ምቾትን፣ ባብዛኛው ደግሞ ሕይወትን የሚጠይቅ ነው ትግሉ።

የሰሞኑን የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛውን ምሥራቅ ህዝባዊ አመፆች አስታኮ፣ በኢትዮጵያም ለአመታት ቦግ ብልጭ እያለ ታምቆ ቆይቶ መፈንዳቱ ከማይቀረው የሕዝባችን እምቢታ ጋር በተያያዘ ብዙ ትግል አሰናካይ ተግባራት እየተስተዋሉ ነው። "እሬ በል ታጋይ!" የሚያሰኙ።

እንጉል ትግልን ጎጂ ስራዎች የትኞቹ ናቸው? ለምሳሌ፣

1. በይፋ ቀንና ቦታ ተጠቅሶ (ግንቦት 20፣ ጠዋት ሶስት ሰዓት፣ መስቀል አደባባይ) የተጠራው ሰልፍ፣

2. ሕዝባዊ እምጽ ሲነሳ መደረግ አለባቸው ተብለው በይፋ የተዘረዘሩት ጉዳዮች፣

3. በምስጢር መጻፍ ይገባል በሚል ዝርዝር ኮድ በይፋ መቅረቡ፣

4. ተሞክሮ የከሸፈን ዘዴ ነፍስ ለመዝራትና አላስፈላጊ ድርጅትን ማቋቋም፣

5. ቀደም ትግልን የጎዳን ክለልተኛነት አሁንም ማንጸባረቅ

ለሰው በላው መለስ ዜናዊ በዚህ ቀን እዚህ ቦታ ወታደርና ታንክህን አሰልፈህ ጠብቀን ማለቱ የሕዝብን ትግል ባይመለከት ኖሮ እንደቀልድ በተወሰደ ነበር። ግና አሳዛኝ እና ጎጂ ድርጊት ነው። ሕዝባዊ እመጽን በተመለከተም ተጨባጭ ዝርዝሮችን ወያኔዎች በኮተሙበትና በተደበቁበት በየፓልቶኩ እና ፌስቡኩ መለፈፉ ሳይከፈሉ ለወያኔ ሎሌ መሆን ነው። ግንቦት 20 በተባለው ቦታና ሰዓት እንገናኛለን ብላችሁ ፈርሙ ጥሪም ከጥራዝ ነጠቅነት አልፎ ትግል ላይ ቀላጅ ነው። ሳያውቁት የተሳሳቱ ወገኖች አንዳንድ ጊዜም "ሙያ በልብ ነው!" የሚለውን የቆዬ አባባል ማስታወስ አለባቸው። የትግሉም ሜዳ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው ሀገር ቤት እንጂ አሜሪካ ወይም አውሮፓ አይደለም። ድልድዩ ጋ እንገናኝ ቀጠሮ በነዚህ የውጭ ቦታዎች/ ሀገሮች ያዋጣ ይሆናል እንጂ በኢትዮጵያ ግን ጥፋትን መጋበዝ ነው። ወይስ ይህን ይፋ ጥሪ እናፋሹ ራሱ ወያኔ ነው? የሱዳኑ አልበሽር በተቃዋሚ ስም በፌስ ቡክ ቀንና ቦታ ወስኖ የተቃውሞ ጥሪ በማድረግ ለአመጽ የተሰባሰቡ የዋሃንን እንዳሳሰረው የወያኔ የተንኮል ወጥመድ ላለመሆኑስ ምን ማረጋገጫ አለ? የሕይወትን መስዋዕትነት ሊያስከፍል

ወደሚችል ትግል ሲገቡ የጠሪውን ቡድን ማንነት መጠየቅ የጥንቃቄ ሀ ሁ ነው።

ሕዝባዊ አመጽ ሲደረግ በዚህ የምስጢር አጻጻፍ ተጠቀሙ ወዘተ ብሎ በይፋ ማቅረቡ ደግሞ የምስጢር አሰራርን ሀ ሁ ያፈርሳል። የምስጢር አጻጻፍ ዋናው ምስጢርነቱ ምስጢር መሆኑ ነው። ያወቁ እየመሰላቸው በይፋ ይህን የምስጢር አጻጻፍ ስልት ተጠቀሙ ባዮች በጣም የተሳሳቱ ናቸው። ስለዚህ አደብ እንግዛ!

ከዚህ ሌላ ግን በአሁኑ ጊዜ ያሉ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች መተባበር ሲገባቸው ከዚህ በፊት ተሞክረው የከሸፉ ድርጅቶች (ኮተት የተባለው ለምሳሌ) እና ዘዴዎች ( የዶክተር አባተ ካሳ የገንዘብ ስብሰባ ዘዴ) ነፍስ ሊዘሩ መሞከራቸው ግራ አጋቢና ሊጠራ ያለውን አደፍራሽ ናቸው። የአንድ ወዳጄን አባባል ልዋስና "በየኪሳቸው ዘውድ ይዘው የሚሄዱ ሰዎች" የየራሳቸውን ቡድን እየፈጠሩ የተቃዋሚውን ወገን እዚያና እዚህ ሊበታትኑት፣ ሃይሉንም ሊያሳስት አይገባም።

ተተኩሶ ያውም የከሸፈ ጥይትም ዳግም ሊቀባበልና ሊተኮስ አይችልም። ከዚህ በፊት የከሸፈን እነግን አቃፊ የትብብር ጥረትም በዚያው በሻዕቢያ አጋፋሪነት ይካሄድ ማለት ስህተትን መድገም ነው። አሁንም የተወሰኑ ድርጅቶችንና ስብስቦችን ያገለለ ውጥን ሁሉ መጨረሻው ከቶም የሚያምር አይሆንም። ከሁሉም በላይ ግን የሀገራችን ትግል የሚመራው እዚያው  በዚያው እንጂ ከአሜሪካ አውሮፓ አለመሆኑን መገንዘብም ያስፈልጋል። ይህን በተመለከተ በሀገር ቤት በትግሉ ቦታ እንገናኝ ብሎ በደፈናው መቃጠሩ እና በትግሉ በተግባር ለመሳተፍ መነሳቱ አግባብ ያለው ይሆናል። የሀገራችንን ተጨባጭ እውነታ መዘንጋት የለብንም።